ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አስር ረከዓዎችን ሸምድጃለሁ።

ከኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አለ: "ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አስር ረከዓዎችን ሸምድጃለሁ። እነርሱም ከዙህር በፊት ሁለት ረከዓ፣ ከዙህር በኋላም ሁለት ረከዓ፣ ከመግሪብ በኋላ ቤታቸው ውስጥ ሁለት ረከዓ፣ ከዒሻእ በኋላም ቤታቸው ውስጥ ሁለት ረከዓ፣ ከሱብሒ ሶላት በፊት ሁለት ረከዓ ናቸው። የሱብሒ ወቅት ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዘንድ የማይገባባት ሰአት ነበረች። ስለሰአቲቱም ሙአዚኑ
አዛን ያለ ጊዜና ጎህ የወጣ ጊዜ ሁለት ረከዓ ይሰግዱ እንደነበር ሐፍሷ ነገረችኝ።" በሌላ ዘገባ ደግሞ "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና
ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከጁመዓ ሶላት በኋላም ሁለት ረከዓ ይሰግዱ ነበር።" [ሶሒሕ ነው።] [በሁሉም ዘገባዎቹ ቡኻሪና ሙስሊም ተስማምተውበታል።]

ዐብደላህ ቢን ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የሸመደዱትን አስር የሱና ረከዓዎች ገለጹ። እነዚህ ሱናዎች "ሱነን አርረዋቲብ" (ከግዴታ ሶላት በፊት ወይም በኋላ የሚሰገዱ ሱና ሶላቶች) ተብለው ይጠራሉ። ሁለት ረከዓ ከዙህር በፊትና ሁለት ረከዓ ከዙህር በኋላ፤ ከመግሪብ በኋላ ሁለት ረከዓ ቤታቸው ውስጥ፤ ሁለት ረከዓ ከዒሻ ሶላት በኋላ ቤታቸው ውስጥ፤ ከፈጅር በፊት ሁለት ረከዓ ይሰግዱ ነበር። ይህም አስር ረከዓ ሞላ። ከጁመዓ ሶላት በኋላም ሁለት ረከዓ ይሰግዱ ነበር።

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/3062